የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ — ታህሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 11
ADDIS ABABA – 17th December, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፹፱ ዓ·ም·
የተሻሻለው የሎሜ አራት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...... ገጽ ፪፻፺፪

## CONTENTS

Proclamation No. 54/1996
Revised Fourth Lome Convention Ratification Proclamation ...... Page 292

## አዋጅ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፹፱
## የተሻሻለውን የሎሜ አራት ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የተሻሻለውን የሎሜ አራት ስምምነት ኢትዮጵያ እና የተቀሩት ወገኖች እ·ኤ·አ· ኖቬምበር ፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ሞሪሽየስ ላይ ስለተፈራረሙ፤

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው በተፈራራሚዎቹ ሀገሮች ሲጸድቅ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሻሻለውን ስምምነት ታህሳስ ፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «የተሻሻለው የሎሜ አራት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፹፱» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

እ·ኤ·አ· ኖቬምበር ፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ሞሪሽየስ ላይ የተፈረመው የተሻሻለ የሎሜ አራት ስምምነት ጸድቋል።

፫· **የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥትና የግል አካላት ጋር በመተባበር የተሻሻለው የሎሜ አራት ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## PROCLAMATION NO. 54/1996
## A PROCLAMATION TO RATIFY THE REVISED FOURTH LOME CONVENTION

*WHEREAS,* the Agreement amending the Fourth Lome Convention was signed by Ethiopia and the other Contracting Parties in Mauritius on November 4, 1995;

*WHEREAS,* the Agreement enters into force subject to ratification by the signatory States;

*WHEREAS,* the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 17th day of December, 1996;

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
   This Proclamation may be cited as the "Revised Fourth Lome Convention Ratification Proclamation No 54/ 1996."

2. *Ratification of the Agreement*
   The Agreement signed in Mauritius on November 4, 1995 to amend the Fourth Lome Convention is ratified.

3. *Power of the Ministry of Economic Development and Cooperation*
   The Ministry of Economic Development and Cooperation is hereby empowered to implement the Revised Fourth Lome Convention in cooperation with the concerned governmental and private organs.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 1·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

4· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 17th day of December, 1996.

Done at Addis Ababa, this 17th day of December, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

lome2/03